ከገብሩ አድጋቦ ሕዳር 16-2000

ፍሎረንስ-ጣሊያን

# «ለውጥ ፈላጊ?! አደግዳጊ!»

**የባንድነት ፋና ወጊ!**

**የአንጅነት፤«ለውጥ-ፈላጊ»**

**ወኔ-ቢስ አረግራጊ**

**ቀበሮ! ወዳጅ ወጊ**

**ወንድም-ከወንድም፤አዋጊ**

**ሃሞተ-ቢስ፤አስወጊ**

**ዐዲስ-ልክፍት፤ወኔ-ዘጊ**

**ተልባ ተሙለጭላጭ፤ሰራጊ**

**በሕልም አ-ራ-ጊ**

**ስልጣን-አጥ፤ስልጣን-ፈላጊ**

**ርባነ-ቢስ፤ጥርግራጊ**

**«ለውጥ-ፈላጊ?!» አደግዳጊ፡፡**

አቤት! ደሞ አቤት!

«ፓራዳይም-ሺፍት?!»

አዲሱ የትግል ስልት

ከመለስ ጉአሮ ለመሸፈት?

በ ወያኔ ቃሬዛ ለመተኛት?

«ለመጫወት ባልና ሚስት?»

ምን የሚሉት ውርደት?

የቁም ቅዠት!

ተራ! ተራ! ቅጥፈት፡፡

ደሞ!

«ሜይን-ስትሪም-ፖለቲክስ»

ምንትስ! ምንትስ!

አ-ደ-ገ-ኛ፤ የስልጣን ሱስ!

መጎንበስ! መ-ል-ከ-ስ-ከ-ስ

ታሪክ-ማርከስ፤እዕርም-መንከስ

የፈሪ ሆድ፤ ፈረስ! ፈረስ!

ል-ፍ-ስ-ፍ-ስ፤ግብስብስ!

ቀኝ-ሁዋላ፤መገስገስ

ከአንገት በላይ፤መመንኮስ

ወያኔን በደንደስ?

ሕዝብ ይጎንበስ

ዕኔ ልንገስ! ዕኔ ልንገስ!፡፡

«የበጋሻው» አንጃ! ግራንጅ!

«ዲፕሎማቲክ-ላንጉኤጅ?!»

ምሎልናል በገሃድ

«የ ኦቶዋውን» መዘላበድ

በቁም ማበድ

የክሕደቱን ወርድ

ከነጫጭባ ማርገድ

«የሱ! የሱ! የግል ነው»

«ሊሕቅና» ተገቢ ነው!

«በሃማ ና ግን በሌላው»

ለሃገር የተሞገተው

ለዓርነት የተፃፈው

«ለቃኤል! ለጌታቸው!»

ሃጢአትም፤ኩነኔም ነው

በድርጅትም መግባት ነው

አ ይ ጌታቸው! አ ይ ገምድለው!

መፎዝ ነው!? ማፌዝ ነው?!፡፡

**አለ ገና! አለ ገና!**

ዕድሜ ደጉ፤ ያሳያልና

«የብተናው ፍልስፍና፤

የፍልስፍናው ብተና»

የጌታቸው በገና

በ ዕብሪት ተወጠረና

በቅዠት ተሰቀለና

«በመሰልጠን» ታጀለና

«ትግል በቃኝ! ዕግሬ አውጪኝ!

ያለ ከዳተኛ! 17 ዓመት የተኛ!

የሞቅ-ሞቅ ዐርበኛ!

ቀን ጠባቂ ዳተኛ!»

የፀጋዬን፤የአበራሽን
የአሰፋ ማሩን
የተስፋዬ ታደሰን
የሺበሬ መስዋዕትን
መገንዘቢያ ነሳውን?!
ወይስ የናቶች የሲቃ ጩኸት
ቺከጎ መሰማት ነበረበት?
አለን አፉን ሞላና
የወያኔ ጎጠኛዉን
አከርከሪ የሰበረዉን
አባ-ዕምቢዮ «ሱናሜውን
«ለ 17 ዓመት!
ባዶ ዘራፍ!
ባዶ ጩኸት!»
አለና ቀለደበት
አወይ ትዕቢት!
አወይ ዕብሪት!፡፡

## ይልቅስ!

ዓይባባ! ዓይባባ! ሆድህ
«በጋሻው» አንጃው ፤ ያጦዘህ!
ተመለስ ወደ ሕሊናህ
አትደር ያለዕቤትህ
አትሂድ ያለመንገድህ
ቀኑ ሳይጨልምብህ
ቁልቁለቱ ሳይበዛብህ
መውጪያው ሳይርቅህ
ማጣፊያው ሳያጥርህ
መባነን ነው ፈጥነህ
አይ! ይ! «ዓይኔን ግንባር ያርገው! ታልህ»
ዕ-ን-ደ-ፍ-ጥ-ር-ጥ-ር-ህ!!

ቸር ይግጠመን